ተያያዥ፤ የነፍስ ወከፍ ዕቅድ መመሪያ

# ኖርዌጅኛ ቋንቋ እና የማኅበራዊ ኑሮ/samfunnskunnskap ለሚማሩና የአገር ማላመጃ ፕሮግራም /introduksjonsprogram (ኢንትሮ) ላይ ለሚሳተፉ ሰዎች የሚሆን የነፍስ ወከፍ ዕቅድ መረጃ

እርስዎና ኮሚነው በጋራ ሆናችሁ፥ ለእርስዎ ኖርዌጅኛ ቋንቋ እና የማኅበራዊ ኑሮ ለሚማሩና ኢንትሮ ፕሮግራም ላይ ለሚሳተፉ፥ አንድ የነፍስ ወከፍ ዕቅድ ታዘጋጃላችሁ።

የነፍስ ወከፍ ዕቅዱ በእርስዎና በኮሚነው መሐል የእርስዎን ትምህርት የሚመለከት የትብብር ውል ነው።

የእርስዎ ዕቅድ፤ እርስዎን የሚመለከት ውሳኔ እና ሕጋዊ ሰነድም ነው።

የማኅበራዊ ኑሮ ትምህርቱ ስለ መብቶች፥ ስለ ግዴታዎች፥ ስላሉት ዕድሎችና ስለ ኖርዌይ ማኅበረሰብ ዋና ዋና እሴቶች መረጃ ይሰጥዎታል።

የትምህርቱ ዓላማ በተቻለ ፍጥነት ወደ ሥራ መስክ ወይም ወደ ትምህርት እንዲሰማሩ እና በኢኮኖሚ ራስዎን ችለው በኖርዌዩ ማኅበረሰብ ውስጥ በንቃት ለመሳተፍ እንዲችሉ ለማድረግ ነው።

## ስለ ነፍስ ወከፍ ዕቅዱ

ሥልጠናው ለእርስዎ የተቀናጀ ከመሆኑ በተጨማሪ፥ ቀድሞ የነበርዎ ትምህርትና የሥራ ልምድ፥ የሙያ ብቃትና ሌላም የእርስዎ የትምህርት ዕቅድ ላይ ፋይዳ ያላቸው መረጃዎች ከግምት ባስገባ ፍኖተ ዕቅድ ላይ የሚመሠረት ነው።

የእርስዎ ዕቅድ በተቀረጸው ፍኖተ ዕቅድ የግምገማ ውጤት እና ለእርስዎ በሚያስፈልግዎት ነገሮች ላይ የሚመሠረት ይሆናል። የእርስዎም የትምህርት ዓላማ በዚህ ጥናት ውጤት ላይ የተመሠረተ ነው።

ይህ የእርስዎ ዕቅድ  ስለ ትምህርትዎ ተጨባጭ የሆነ ዓላማ፤ ዓላማው ላይ ለመድረስ የተሰጠውን የጊዜ ገደብ፤  ለእርስዎ የተመደበሎትን ሰዓታት ቁጥር፤ እንዲሁም መቼ እና የት ትምህርቱ እንደሚካሄድ የሚገልፅ  ነው።  የእርስዎ ዕቅድ ከእርስዎ ጋር በመተባበር የሚዘጋጅ ነው።

በትምህርት ተሳትፎዎ ላይ ተጽዕኖ ሊያደርጉ የሚችሉ የማኅበራዊ ኑሮ ወይም የጤና ተግዳሮትዎች ካሉ እነሱም ከግምት መግባት ይኖርባቸዋል።

የሚጠበቀው ደረጃ ላይ እንዲደርሱ ትምህርቱ ከጅምሩ አቅጣጫ መያዝ አለበት። በዚህ መንገድ እጅግ የላቀ ውጤት ያገኛሉ። ትምህርቱ እርስዎ ህፃን ልጅ የሚንከባከቡ ከሆነ ወይም ሥራ የሚሠሩ ቢሆንም ወይ ሁለቱም፤ ከእርስዎ ሕይወት ሁኔታዎች ጋር እንዲጣጣም ሆኖ መቀረጽ አለበት። የእርስዎ ዕቅድ ከሙያና ከተግባራዊ ፍላጎትዎ ጋር የተጣጣመ ይሆናል።

ኮሚነው እስከ ቢ2 (B2) ደረጃ በደንብ የተወሰነው በ600 ሰዓቶች የጊዜ ገደብ ውስጥ የሚደረስ ከሆነ፥ እንዲሁም እስከ ቢ1 (B1) ደረጃ በደንብ የተወሰነው በ3000 ሰዓቶች የጊዜ ገደብ ውስጥ የሚደረስ ከሆነ፥ ትምህርቱን የመጋበዝ ግዴታ አለባቸው።

በትምህርት ላይ እያሉ፥ ኮሚነው የእርስዎ የግል ዕቅድ እንዴት እየሄደ እንደሆነ ለማየት ከእርስዎ ጋር ውይይቶች ያደርጋል። አስፈላጊ ከሆነ፥  ለምሳሌ በሕይወትዎ ላይ ትልቅ ለውጥ ካለ፤ ዕቅዱ ሊቀየር ይችላል። በእርስዎ የግል ዕቅድ ላይ ታላላቅ እና ጠቃሚ ለውጦች ካሉ፤ አዲስ ዕቅድ ለማውጣት ይችላል።

ዕቅድዎን የማይከተሉ ከሆነ፥ ወይም ዕቅዱን መቀየር ከፈለጉ በአስቸኳይ ጉዳይዎን ከሚከታተለው ሰው ጋር መነጋገር ይኖርቦታል።

## የነፍስ ወከፍ ዕቅድዎ ላይ ቅሬታ ማቅረብ ይፈልጋሉ?

ስለ ትምህርትዎም  ሆነ ወይም ስለ የነፍስ ወከፍ ዕቅድዎን በተመለከተ ቅሬታ ለማቅረብ ይችላሉ። አዲስ የነፍስ ወከፍ ዕቅድ ከተሰጠዎት፤ ስለ ለውጡ መልዕክት ከደረስዎት ቀን ጀምሮ በሶስት ሳምንታት ውስጥ ይግባኝ ማለት ይችላሉ።

ይግባኝ ለማለት የሚፈልጉ ከሆነ የሚከተሉት መሟላት ይኖርባቸዋል፤

- ስለ ዕቅዱ መልዕክት ከደረስዎት ግዜ ጀምሮ በሶስት ሳምንት ውስጥ ቅሬታዎን ማቅረብ
- የእርስዎ ዕቅድ ላይ ውሳኔ ባሳለፈው ኮሚነ ወደ ሚመለከተው ክፍል ቅሬታውን ማቅረብ
- የሚቃወሙትን ነገር በጽሑፍ ማቅረብ
- በቅሬታው ማመልከቻ ላይ ፊርማ ማኖር

አንድ ወኪል በእርስዎ ፋንታ ቅሬታዎን ሊያቀርብልዎት ይችላል። ሌላ ሰው እርስዎን ወክሎ ቅሬታዎን እንዲያቀርብልዎ ከፈለጉ ፥ በጽሑፍ ውክልና ሊሰጡት ይገባል። የውክልና ሰነዱ ተወካዮ እርስዎን ወክሎ ምን ማድረግ እንደሚችል መግልጽ አለበት። ጠበቃ ካለዎት የውክልና ወረቀት አያስፈልጎትም።

## በኢንትሮ ፕሮግራም ላይ ተሳታፊ ነዎት?

**በኢንትሮ ፕሮግራም የሚሳተፉ ከሆነ፤ በነፍስ ወከፍ ዕቅዱ የሚሰጥ የኖርዌጅኛ ቋንቋ ትምህርት በኢንትሮ ፕሮግራሙ ከሚሰጠው ግላዊ ዕቅድ አንድ ክፍል ነው።**

**ስለ ኖርዌጅኛ ቋንቋ እና ስለ ማኅበራዊ ኑሮ ትምህርት፥ እንዲሁም ስለ ነፍስ ወከፍ ዕቅዱ የበለጠ መረጃ በማኅበራዊ ኑሮ ፕሮግራም ሕግ ላይ ያገኛሉ። ሕጉን እና መመሪያውን በ www.imdi.no እና በ "Kompetanse Norge" ድረ ገጾች ላይ ያገኛሉ።**

**መልካም ዕድል ከትምህርትዎ ጋር!**